የአባይ ፖለቲካ ሲደርቅ፥
የዘመዴነህ ብቅ ብቅ ፥
የምሁር ዐይነ ደረቅ

ከገዳ ውቤ

መቸም እንግሊዝኛ ማንብነብ ምሁር ካስባለ፥ በልጅነት ያንጎራጎርነው EYO DENOTE ዓይነቱን አየ ጣሊያንኛ ሲችል አስብሎን ነበር። ጀርመንኛ ትንሽ ትንሽ ይችሉ የነበሩት አክስቴ፥ ነፍሳቸውን ይማርና፥ ማንበብና መጻፍ ባይችሉም ግን ጀርመን ትምህርት ቤት ለብዙ ዘመን ፅዳት ይሰሩ ስለነበር አንዳንዴ ባማርኛቸው ላይ " ታንከሽ " ይሉ ስለነበር ልክ እንደ አልበርት አንስታይን ይታዩ ነበር፥ በሰፈርተኛው ሁላ !

"ምሁር ማለት" ይላሉ ዕውቁ አባት አርበኛ ኮ/ሎ አስናቀ ዕንግዳ፥ " ምሁር ማለት ተማረ ማለት ነው፥ መማር ደግሞ ድንቁርና የፈጠርውን የውስጥን ጨለማ በዕውቀት ሻማ መግፈፍ ነው ። ለዚህም ነው አንድ ሰው ተማረ ሲባል ምህረትን አገኘ፥ ድንቁርናን ገፈፈ የሚባለው" ሲሉ አድምጫቸዋለሁ ። ትክክለኛ አባባል !

አንዳንድ የተማሩ ግን ህሌናቸውን በጥቅም አውርው ምህረት ያለገኙ የተበራከቱበት ዘመን ላይ ደርሰናል።

ለዚህች አጭር ትችት መነሻየ፥ ባለፈው ቅዳሜ ከተሰዓት በኋላ በዋሽንግቶን ዲሲ ዋርድማ ማሪዮት ሆቴል የተከታተልኩት የማያስቅ ግን ፥ አስለቃሽ የእንግሊዝኛ ኮሜዲ ድራማ ውጤት ነው። ለማስተዋወቅ ከተፈቀደልኝ፥

አዘጋጅና ደራሲ ፦ የወያኔው አክተር መለስ ዜናዊ
ማናጀሮቹ፦ ባዕዳን ወራሪዎች
የመድረኩ አቀነባባሪና ተዋናይ ፦ ምሁሩ ደላላ ዘመዴነህ ንጋቱ
ተመልካች ፦ ኢትዮጵያኖች

Fair Fax Africa Fund
ተብሎ የተነገረለት አገራችሁ እንዴት መዋዕለ-ነዋያችሁን እንደምታፈስሱ አመቻቸለሁ ባዩ አንድ ሃሳዊ ኢኮኖሚስት በጠራው ስብሰባ ላይ ያወራው ወይም ይነግረን የነበረው ንግግር የክፍለ- ዘመኑ ታላቅ በቀቀን ካድሬ አስመስሎት ውሏል። ( ፋና ሬደዮ በእንግሊዝኛ ) በጣም ብዙ እንኳን ከተናገረው ይወሰድ ከተባለ ውሎ ማደርን ይሚጠይቅ ዕሁፍ ማቅረብ ይቻላል። በእኔ በኩል፥ በሰውየው በእንግሊዝኛ ጀምሮ የጨረሰው፥ ንግግሩ፥ኢትዮጵያን ላላወቀ ነጮቹ ( አለቆቹ ) ማርስ ላይ ጠፍጥፈው የሰሯት እንጅ፥ ይህች የኛዋ ፥ የማንም መቀለጃ የሆነችው የምሥራቅ አፍሪካዋ ኢትዮጵያ አትመስልም ነበር ።

" ሀገራችሁ ገብታችሁ፥ ግንባታ ፥ ማዕድን ማውጣት፥ ለኃይል ፥ ለአግሮ-ኢንዱስትሪ ለመሳሰለው ኢንቨስት አድርጉ" ነው የሰውየው መልዕክት ። ሀቁ ግን፥ የከሰረው የዓባይ ወንዝን የድረቀት ፖለቲካን በዘመዴነህ ተጠቅመው ፥እንደ ወንዝ ለማርጠብ የወያኔ ሃርነት ትግራይ አዲስ ቧልት መሆኑ የሚታወቀው።

ተናጋሪው ፥ ኢትዮጵያ ከ3 እና 5 ዓመት በኋላ በኢኮኖሚ ከቻይናና ከህንድ ቀጥለስ ከዓለም 3 ኛ ትወጣለች ፥ ከአፍሪካ 1ኛ ትሆናለች ስላለ ወይም በአሁኑ የሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ስንመዝነው ንግግሩ ቅዠት ስለሆነም አይደለም ደረቅ ዎያኔ ወይም ርጥብ ምሁር

ወይም ሆዳም እከሌ ያሰኘው፡፡ ልክ እንደ በቀቀን ካድሬ መለስ ዜናዊ የተናገረውን ወይም የቃላት ድፈረቱን እንዳለ ስለሚያስተጋባም ጭምር ነበር፡ መቸም ኢንቨስተር ( ቢንቬደር) መልክ ሆኗል በኢትዮጵያ ውስጥ ፡፡ ስለዚህም በምሁሩ ደላላ የደሰኮረልን የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር 100- 120 ሚሊዮን በቅርቡ ይደርሳልና ለቆሻሻ ማራገፊያ ኮንቴነር ይመቻል፡፡ ዓይነቱ ግፈኛ አባባልን ከአንድ ኢትዮጵያዊ ከሚመስል ሰው መሰማቱ ምንኛ ሕዝባዊና ሀገራዊ ፍቅር የሚሉት ምትሀታዋ ቃል.እየጠፋ ግልኝነትና የሀገር አሻሻጭ ደላላነት እንደተስፋፋ ያስተዋልኩበት ቀን ነው ፡፡

ፀረ ኢትዮጵያዊው የወያኔ ሃርነት ትግራይ መላሱ ዜናዊ በአንድ ወቅት፥ በቅርቡ ስለ መሬት ለባዕዳን መሸጥ ፥ ከ 4 ሚሊዮን ሄክታር በላይ ል መሬት ለህንድ፥ ለቻይና ፥ ለሱዳን ለነጩ ፥ ለዐረቡ ለምን ይሸጣል ? ተብሎ ሲጠየቅ ያስመለስው ( የመለሰው) መልስ እንዲህ የሚል ነበር፥ቃል በቃል፥

> " ማልቀስ ለተሸጠው 4 ሚሊዮን ሄክታር ሳይሆን፥ ገዥ ላጣው 70 ሚሊዮን ሄክታር መሬት ነው " ብሏል መልስ ዜናዊ

ስድ- አፉ መለስ ፥ በኢትዮጵያ ላይ ያቀረሸውን የጥላቻ ቅርሸት ተመልክተናል፡፡ የእርሱ አባባል አይገርመንም፥ የእርሱ ነውና ! እርሱ በትግርኛ የነገረንን የእኛ ትርጁማን ምሁሮች ወይም ሞሮኖች፥ በአማርኛና በእንግሊዝኛ ሲተረጉሙልን በመድረክ ላይ ስንሰማ ፥ ምነው ቴዎድሮስ ( ቴዲ) መቃብር ፈንቅሎ በተነሳ ያሰኛል፡፡ ምንም እንኳን በቅርቡ ሚሊዮን ወጣት ቲዎድሮሶች እንደሚከሰቱ ጥርጣሬ ባይኖረንም !

ዓፄ ቴወድሮስ የማረኳቸውን በሚሲዮን ስም የመጡ የእንግሊዝ ሰላዮችን አስረው ወደ መጡበት ሲመልሱ የሰጡት ትእዛዝ፥ " በምፅዋ በኩል አሳፍሯቸው፡፡ ግን ከመሳፈራቸው በፊት የሀገሬን አፍር ይዘው እንዳሄዱ ጫማቸውን አሳጥባችሁ ስጧቸውና አባርሯቸው " ነበር ያሉት፡፡ አባባሉ አፈ ታሪከ ሳይሆን፥ ዕውነት ነው፡፡

ያለፈው ሳምንት የመለስ ዜናዊ አፍ ሆኖ ይናገር የነበረው ባለተልዕኮኛው ምሁር፥ ይህንን ቢያውቅ ምን ያህል ደስተኞች እንሆን ነበር፡፡

ፀለምቴዎች፥ አየ ጣሊያን አየ ጣሊያን አሉ አሉ የሆኑ ቻይናዎችን አይተው፡፡ አንዱ ሰልጡን ነኝ ያለው ወጣት ልጃቸው ግን " አባባ ይሄ እኮ ቻይናዊ ነው " ሲላቸው፥ "አየ ይህችን መቼ አጣን ጃል ነጭ ዐይኗን አጥባ ስትመጣ " ያሉት አባባል እንደ ዘበት አይቆጠርም ፡፡ የጥንት አባቶቻችን እናቶቻችን ፀረ ቅኝ አገዛዝ መንፍስ አድሯባቸው እንጅ፥

> "ትላንት በሚሲዮን ስም ዛሬ በኢንቨስተር፥
> ዝም ትላለህ ወይ ሀገር ሲወርር ! " እንዳለው አዝማሪው

ታዲያ አልተማረም የሚባለው የሀገራችን አርሶ-አደር ቀናዒ የሆነላትን ሀገር ምነው ምሁር ነን ባዮች እንደ ሳምንቱ ዓይነት ተናጋሪ ነሆለሉ ?

አኝዋኮች "የጋምቤላ መሬት የኢትዮጵያ ሀብት ነውና ለማሌዥያ ቱጃሮች አይሸጥም በማለታቸው በነመለስ ዜናዊ አዝማጅነት በወያኔው ዶ/ር ባርናባስ ፊታውራሪነት ጦር ተመዝዞባቸው ከ 5000 በላይ ከተጨፈጨፉ ገና 10 ዓመት እንኳን አልሞላም፡፡ ብቅርቡስ 50 ሺ አባዎራዎችተፈናቅለው ያ ድንግል መሬት ለህንድ ተሸጦ የለ! ያውም ሄክታር በስ ሙኒ ! አቶ ዘመዴነህ በላይነህ ግን ባለፈው የዲሲ ስብሰባ " ይህን አላውቅም እኔ የተማርኩት ኢኮኖሚከስ ነው ፡፡ ስለ ሰብዓዊ መብት አያገባኝም፡፡ " ብሎ የነገረን፥ ዛሬ ለኢንቨስተሮች ተብላ

FOR SALE !
የተለጠፈባት ውድ ሀገራችን ኢትዮጵያ ተከላካይ የላትም ተብሎ እየተንደረደርን እየሄድን የሰው ቤት እያስፈረስን ወፍጮና ቪላ የምንተክል ተላላዎች ካለን ዛሬ ባይሆን ነገ

" የማን ቤት ጠፍቶ የማ ሊበጅ የአውሬ መፈንጫ ይሆናል እንጅ " የሚለው ጥንታዊው የሀገር ፍቅርና ክብር የወለደው ወኔ ሲቀሰቀስ ቻይናውም÷ ህንዱም÷ ዐረቡም÷ ነጩም ÷ ደላላው ምሁር ዘመዴነህም ማንም ማንንም አያስጥል፡፡ ከሁሉ በፊት ኢትዮጵያዊ መንግሥት በወያኔ ከርሰ–መቃብር ላይ መመስረት አለበት፡፡ ከልማት በፊት ነፃነት ቀዳሚ ይሁን፡፡ የኢትዮጵያ አርሶ–አደር ያስተማረን እንድንናገርለት እንጅ እንድንነጋግርበት አይደለም ! የኢትዮጵያ ሕዝብ ያስተማረን እንድንመሰክርለት እንጅ እንድንመስክርበት አይደለም ! ፡፡

የኢትዮጵያን ሉዋላዊነት በደማችን እናስከብራለን ፡፡

ሽሮ በነፃነት ከሰረቁት ዶሮ
ሀገር ይሸጥ ይላል የምሁር ደንቆ !

ኢትዮጵያ ሀገራችን ዘለዓለማዊት ናት !